**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ**
**አሜን**

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
## ዓለም አቀፋዊ የምዕመናን ጉባዔ ውሳኔ

1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፋዊ የምዕመናን ጉባዔ ከህዳር 14 ቀን እስከ ህዳር 16 ቀን 1999 (November 23-25,2006) በዳላስ ክተማ ቴክሳስ ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍአሜሪካ በደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል የስብስባ አዳራሽ በአካሄደው ጉባዔ፤

2. በምሁራን ባለሙያዎች የተደገፉ ጥናቶችን፤ ሁኔታዎችንና ድርጊቶችን ሁሉ ከመረመረና ውይይቶች ካካሄደ በኋላ፤

3. **የሚከተሉትን ግንዛቤዎች ወስዶ ማለትም፡<**

3.1 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሀገራችን ውስጥ ስብከተ ወንጌል ለጠቅላላው ሕዝብ እንዲዳረስ የምታደርገውን ጥረት፤ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ሕዝብና በጠቅላላውም ለዓለም ሕዝቦች ሰላም እንዲወርድ ፍቅርና መተባበር እንዲዳብር የምታደርገውን ጾም ጸሎት ሱባዔና ምህላ ተገንዝቦ

3.2 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጽላተ ሙሴን ከእግዚአብሔር ለዓለም ሕዝቦች በአደራ ተቀብላ አቆይታ በአሁኑ ጊዜ የታቦተ ሕግጋቱን ቡራኬና ወንጌሉን ከአጽናፍ እስከአጽናፍ እንዲዳረስ በአሜሪካ በአፍሪካ በአውሮፓና በአውስትራሎኤስያ የጀመረችውን ጉዞ አበረታችነት በመመልከት

3.3 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኤኮኖሚና በማህበራዊ ረገድ የብዙ ሰዎች አለኝታና አስተዳዳሪ መሆኗን በማስታወስ

3.4 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ውንጌላዊት ጉዞዋ የሚሰምረው ትምህርቷና ዕምነቷ በሁሉም ቋንቋ ሲቀርብ መሆኑን በመገንዘብ

3.5 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጀርባ አጥንት ሆነው ለዘመናት ያገለገሏት ገዳማትና አድባራት እንዲሁም የአብነት ትምህርት ቤቶች በአሁኑ ጊዜ በመዳከማቸውና እንዲጎለብቱ ማድረግ የሚገባ መሆኑን በማጤን

3.6 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የሚገኘው ጥንታዊ ይዞታዋና ቅርሶቿዋ በአሁኑ ጊዜ የደረሰባቸውን አስጊ ሁናቴ በመገምገም

3.7 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በረጅም ጊዜ ታሪኳ ውስጥ ከልዩ ልዩ ዕምነት ተከታዮች ጋር በመከባበር በመግባባት ሐዋርያዊ ሥራዋን ስታካሂድ መኖሯንና ወደፊትም በዚሁ በሰላም መንገድ ለመቀጠል መነሳሳቷን በማረጋገጥ

3.8 ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአክራሪ ሙስሊሞች የተጠነሰሰው አለመግባባት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዕምነት ተከታዮችና በንብረቷ ላይ የደረሰውን አሰቃቂ ውርጅብኝ በአንክሮ በማጤን

የምዕመናኑ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት እስኪቋቋም ድረስ ለተጨማሪ ማብራሪያና ለጥያቄ የጉባዔውን ሊቀ መንበር
ኤንጂኒር ተረፈ ራስ ወርቅን መጠየቅ ይችላሉ
*በፖሳታ 34 Avenue Blanc, CH-1202 Geneva, Switzerland Email raswork@ties.itu.int*
*በስልክ +41792506313, +41223106715 በፋክስ +41223106739*

3.9 በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የሚደረገው ጥረት ሁሉ አመርቂነት የሚያገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ጳጳሳት፤ ካህናት እንዲሁም የጠቅላላው የምዕመናን አንድነትና ትብብር ሲኖር መሆኑን በመገንዘብ፡>

## 4 የሚከተሉትን ውሳኔዎች ወስደናል፡<

4.1 የጌታችን መድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለዓለም ሕዝቦች ለማደራስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሕልውና የሚጠብቅ ከጳጳሳቱና ከካህናቱ ጉባዔ ጋር ተባብሮ ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚደግፍ አንድ ዓለም አቀፋዊ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ጉባዔ አቋቁሟል

4.2 ጉባዔው በልዩ ልዩ ዘርፎች የቀረበለትን ጥናታዊ ጽሁፎች ተመልክቶ ያወጣውን ራዕይና ዓላማ ዕውን ለማድረግ የሚጠበቅበትንም ሃላፊነት በሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል፤

- 4.2.1 የጠቅላላውን የጉባዔውን ሂደት የሚከታተል አስፈላጊውንም የሰው ኃይል ፤ የገንዘብና ቁሳቁስ የሚያደራጅ አንድ የሥራ መሪ ግብረ ኃይል አቋቁሟል
- 4.2.2 የሥራ መሪው ግብረ ኃይል ጉባዔው የተለመውን መንደርደሪያ ሀሳቦች በመከተል የምዕመናኑ ጉባዔ የሚቋቋምበትንና የሚደረጅበትን ሥራዎች ይሠራል፤ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ አስፈላጊ የመሰሉትንም የሥራ አስፈጻሚ ግብረ ኃይል ያቋቁማል
- 4.2.3 የሥራ መሪው ግብረ ኃይል በአክራሪ ሙስሊሞች ተጠንስሶ በቤተ ክርስቲያናችንና በተከታይ ምዕመናኖቿ እንዲሁም በጠቅላላው በሀገሪቱ ህልውና ላይ የተሰነዘረውን አስከፊ አደጋ ለመከላከል እርቅና ሰላም እንዲሁም መግባባት እንዲሰፍን ተጨባጩን ሁናቴ መርምሮ ሰብስቦ ለሀገር ለወገን ለተቆርቋሪ አትማማች ቤተክርስቲያናትና ለዓለም አቀፍ ድርርጅቶች ያሳውቃል፤ አስፈላጊውም እርምጃ እንዲወሰድ ይከታተላል
- 4.2.4 የሥራ መሪው ግብረ ኃይል በውጭ ሀገር የሚኖሩ ወጣቶች በዕምነታቸው እንዲጠነክሩና በግብረገብነትም የሚያድጉበትን ክርስቲያናዊ ትምህርት የሚሰጥበት ሥርአተ ትምህርትና ማስተማሪያ መጻህፍቶች እንዲዘጋጁ ያደርጋል
- 4.2.5 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በልማት በኩል የጀመረችውን አገልግሎት በተቀናጀና በሰመረ መንገድ ተስፋፍቶ እንዲቀጥል በዕውቀት፤ በገንዘብ፤ በቁሳቁስና በልዩ ልዩ ሙያዎች፤ ምዕመናኑ በያሉበት ለልማት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ጥረት ያደርጋል
- 4.2.6 የአብነት ትምህርት ቤቶች ለቤተ ክርስቲያኒቱ እድገት በጣም አስፈላጊ መሆናቸውን በመገንዘብ ዋሽንግቶን ዲሲ የሚገኘውን የአብነት ትምህርት ቤቶች ማጠናከሪያ ማኅበር ዕውቅና በመስጠት የዓለም አቀፋዊው የምዕመናን ጉባዔ ሁለተኛው ግብረ ኃአይል አድርጎ ወስዶታል።
- 4.2.7 በሀገር ውስጥ የሚገኙትን ገዳማትና አድባራት እንዲሁም በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የሚገኘውን ጥንታዊ ይዞታ የሚጠበቁበትን የሚዳብሩበትን መንገድ ከቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤትና ከኢየሩሳሌም ገዳም ጋር በመተባበር አጥንቶ አስጠንቶ ለሚመለከታቸው ሁሉ በማቅረብ አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድ ይጣጣራል።

የምዕመናኑ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት እስኪቋቋም ድረስ ለተጨማሪ ማብራሪያና ለጥያቄ የጉባዔውን ሊቀ መንበር
ኤንጂኒር ተረፈ ራስ ወርቅን መጠየቅ ይችላሉ
በፖሳታ 34 Avenue Blanc, CH-1202 Geneva, Switzerland Email raswork@ties.itu.int
በስልክ +41792506313, +41223106715 በፋክስ +41223106739

4.2.8 የሰብከተ ውንጌልን እንቅስቃሴ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለማጠናከር እንዲቻል ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመተባበር የአጭርና የረጂም ጊዜ እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ያመቻቻል ።

4.2.9 በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በሚገኙት አባቶች ጳጳሳት መሀከል ያለው አለመግባባት ከእሱም ጋር የተያያዘው የካህናትና የምዕመናን መከፋፈል የምዕመናኑን ጉባዔ እጅግ አስጨንቆታል አሳስቦታልም። በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችንና በተከታዮቿ ምዕመናን ላይ ብሎም በሀገሪቱ ውስጥ በሰው ህይወትና በንብረት ላይ የደረሰውና በመካሄድም ላይ ያለው አስከፊ እልቂት የቤተ ክርስቲያኒቱን መኖርና አለመኖር ስለሚነካ <u>አባቶች ጳጳሳት እንዲሁም ካህናትና ምዕመናን ጊዜያዊ ልዩነታቸውን ወደጎን አድርገው ለቤተክርስቲያኒቱ ህልውናና ለተከታዮቿ ደህንነት ብለው በአንድነት በመተባበር እንዲቆሙ አስቾኳይ ጥሪውን ያስተላልፋል</u>።>

## 5 ምስጋናና የወደፊት ስብሰባ ቀን

የመጀመሪያውን ዓለም አቀፋዊ የምዕመናን ጉባዔ በማዘጋጀትና በማካሄድ በገንዘብ በጉልበት በምክር አስተዋጽኦ ያደረጉትን አዘጋጅ ኮሚቴውን፤ ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናትን፤ ድርጅቶችንና ግለ ሰቦችን አመስግኖ የሚቀጥለው ዓለም አቀፋዊ ጠቅላላ ልዩ ስብሰባ በሚመጣው ዓመት ማለትም በሶስተኛው ሺ ዓመተ ምህረት መጀመሪያ ላይ እንዲጠራ ወስኖ የመጀመሪያው ጠቅላላ ስብሰባ ተነስቷል።

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**

የምዕመናኑ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት እስኪቋቋም ድረስ ለተጨማሪ ማብራሪያና ለጥያቄ የጉባዔውን ሊቀ መንበር
ኤንጂኒር ተረፈ ራስ ወርቅን መጠየቅ ይችላሉ
*በፖሳታ* 34 Avenue Blanc, CH-1202 Geneva, Switzerland Email raswork@ties.itu.int
*በስልክ* +41792506313, +41223106715 *በፋክስ* +41223106739